“ኢትዮጵያ፡ሀገሬ፡ሞኝ፡ነሽ፡ተላላ፣
የሞተልሽ፡ቀርቶ፡የገደለሽ፡በልላ”።*፩፡-

መስከረም፡፰፡ቀን፡፳፻፰፡ዓመተ፡ምሕረት። ገጽ፡፩-፫፡-

# “ሲያዩት፡ያምር፡ሲይዙት፡ይደናገር”።

ሕዝብን፡የበደለ፡መሪ፡ይዋረዳል።




ጭምብል፡መለስ፡ኃይለማርያም።

የትግሬ፡ወያኔ፡አገልጋይና፡አፈ፡ቀላጤው፡የኢሕአዴግ፡ያን፡የመሰለ፡ንግግር፡መግለጹ፡አያስገርምም።ጠቅላይ፡ምሉክ፡(ምኒስትር)፡ኃይለማርያም፡ደሳለኝ፡አጀማመሩ፡የሰይጣኑና፡ከሃዲ፡መለስ፡ዜናዊን፡በማሞገስ፡ራዕዩን፡ሳይበረዝ፡የሚከተል፡መሆኑን፡ምህላ፡ባደረገበት፡ወቅት፡አረጋግጠናል።የከሃዲው፡መለስ፡ዜናዊ፡አገልጋይ፡ስለ፡ነበረ፡“ሲጠሩት፡አቤት፣ሲነግሩት፡ወዴት”፡የሚል፡ስለሆነና፡ቀደምት፡ታሪኩን፡ስንመለከት፡በዐማራ፡ሕዝብ፡ላይ፡የበታችነት፡የሚሰማውና፡ከፍተኛ፡ጥላቻ፡እንዳለበት፡ነው።በመምህርነቱ፡ግዜ፡ያደርግ፡የነበረው፡ልዩነት፡በተማሪዎቹ፡ይታወሳል።እርስ፡በእርስ፡እንዲጋጩ፡ማድረግ፡ይወድ፡የነበረና፡ተንኮለኛ፡መሆኑም፡ይነገራል።አጎብዳጅና፡ዐማራን፡የሚጠላ፡መሆኑን፡ከሃዲው፡መለስ፡ዜናዊ፡እሺ፡ባይ፡አገልጋይ፡ስለሚሆን፡አውቆ፡ወደ፡እርሱ፡አማካሪው፡አድርጎ፡አቀረበው።እርሱ፡ካለፈ፡በኋላ፡የቀሩት፡የትግሬ፡ወያኔ፡ጥርቃሞች፡እነ፡በረከት፡ስምዖን፡በአሻንጉሊትነቱ፡ለመጠቀም፡ጠቅላይ፡ምሉክ፡(ሚኒስትር)፡እንዲሆን፡ተስማሙ።ሁኔታው፡ሲያመቻቸው፡እንደሚፈነቅሉት፡ረጅም፡ግዜ፡አይወስድምና፡አተኩሮ፡ይጠብቅ።



ደመቀ፡መኮንን፡ሐሰን።

“በኢትዮጵያ፡ሥነ፡መንግሥት፡(ፖለቲካ)፡ሥልጣን፡ላይ፡የኢትዮጵያ፡ኦርቶዶክስ፡ተዋኅዶ፡አማኝና፡ዐማራ፡ብቻ፡ሲፈራረቁበት፡የነበረውን፡ሁኔታ፡ሰብረነዋል”።እያለ፡ስብሐት፡ወልደ፡ሥላሴ፡ነጋ፡በሚፎልልበት፡ወቅት፡ጠቅላይና፡ምክትል፡ሆነው፡የመጡትን፡መሪዎች፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡“ሳይቃጠል፡በቅጠል”፡እንዲላቸው፡እናስገነዝባለን።

ሁኔታው፡ኢትዮጵያ፡ከመውደም፡ያተረፈተው’ን፡እስልምና፡እምነተም፡በቁጥጥራቸው፡ሥር፡አድርገው፡ነባሩን፡በመከለስ፡አሕባሽ፡ለሚሉት፡በመከፋፈል፡ወግነው፡ወገኖቻችንን፡በዱላ፡ሲቀጠቅጧውቸው፡ይታያልሉ።ሁለቱ፡የተሾሙበት፡ዋንና፡ምሥጢር፡ዐማራን፣ኢትዮጵያንና፡የኢትዮጵያ፡ኦርቶዶክስ፡ተዋኅዶ፡እምነትና፡ቤተ፡ክርስቲያንን፡በቀንደኛው፡አላሙዲን፡አጋዥነትና፡በአረመኔው፡ከሃዲ፡መለስ፡ዜናዊ፡የተተለመውን፡ትልም፡ለመድፈን፡ነውና፡ሕዝብ፡ግዜ፡ሳይሰጥ፡ሊነቃባቸው፡ይግገባል፡እንላለን።ለዚህም፡ማስረጃው፡ኃይለማርያም፡የጴንጤ፡አማኝ፡መሆኑ፡በይፋ፡ሲታወቅ፤ደመቀ፡ደግሞ፡የአሕባሽ፡አጫፋሪዎች፡እንደሚሆኑ፡እንገምታለን።ለግምታችን፡አመላካቹም፣የእስልምና፡አማኝ፡በሆኑት፡ሰላማዊ፡ወገኖቻችን፡ላይ፡የሚያስደርጉትን፡ድብደባ፡በተንቀሳቃሽ፡ምሥል፡እያየነው፡ነው።ዛሬ፣የእስልምና፡ቅዱስ፡ሲኖዶስ፡(መጅሊስ)፡በመስጊድ፡ሳይሆን፡በየቀበሌው፡እንዲመረጡና፡በእነርሱ፡ቁጥጥር፡ውስጥ፡አስገ

ገጽ፡፪-፫፡-

ብተው፡ነባሩን፡የእስልምና፡እምነት፡ኢትዮጵያ፡እንዳይወድም፡ጥገኝነት፡ሰጥታና፡ተከላክላ፡ያተረፈችውን፡በሽብርተኛነት፡ስም፡አማኙን፡በመከፋፈል፡ለማውደም፡ተዘጋጅተዋል።ያ፡ደግሞ፡



*፩፡- በጀግናው፡ቀኝ፡ጌታ፡ዮፍታሔ፡ንጉሤ፡የተነገረ፡ቅኔ።

## “ኢትዮጵያ፡ሀገሬ፡ሞኝ፡ነሽ፡ተላላ፣ የሞተልሽ፡ቀርቶ፡የገደለሽ፡በልላ”።*፩፡-

የመቀሰፊያቸው፡ስለሆነ፡ከከሃዲው፡አለቃቸውና፡ቄስ፡ገብረመድኅን፡አለመማራቸው፡የሥ ልጣን፡ጥመኞች፡እንጂ፡ለሕዝብና፡ሀገር፡የማያሥቡ፡መሆናቸውን፡በግልጽ፡ያመለክታሉ።ይህ ን፡መሠል፡ሥልጣንም፡በአረመኔው፡ከሃዲ፡መለስ፡ዚናዊ፡የተለገሣቸው፡እንጂ፡ከ፡እግዚአብሔ ር፡ተባርኮ፡የተሰጣቸው፡አለመሆኑን፡ይገንዘቡት።ኢትዮጵያውያን፡ወገኖቻችን፡ብለን፡የትግ ሬ፡ወያኔዎችን፡ባለ፡መጠርጠር፡አስገብተን፡ሃያ፡አንድ፡ዓመታት፡መዓትና፡ልቅሶ፡አመጡብን።ያን፡በደል፡ተመልካች፡አሁን፡ፍርዱን፡በመስጠት፡ላይ፡ስለ፡ሆነ፡ለኃያሉ፡እግዚአብሔር፡ክብር፡ምሥጋና፡ይሁነውና፡በእነርሱ፡የሚደረግብንን፡መከራና፡ሥቃይም፡በቅርቡ፡ያሳልፍልናል።

A)*http://www.youtube.com/watch?feature=player_embedded&v=kazrs5MBHylhttp://www.youtube.com/watch?feature=player_embedded&v=kazrs5MBHyl ሀገሩን፡ለባዕድ፡ጎረቤት፡ፈርሞ፡የሰጠ፡ም/ምሉክ፡አላዩንም።

B)*http://www.youtube.com/watch?feature=player_embedded&v=CJ83ZteVaGQ የእስልምና፡አማኝ፡ወገኖቻችንን፡ይኸን፡ሁልሉ፡ሥቃይ፡ችለው፡ሰላማዊ፡ትግላቸውን፡በመቀጠላቸው፡እያመሠገንን፡እንኮራባቸዋለን።ሌሎቻችን፡በዝምታ፡መመልከ ታችን፡ግን፡እያስተዛዘበን፡ነው።

ኃይለማርያም፣በአዲስ፡መጡ፡የጴንጤ፡ሃይማኖት፡ተከታይ፡በመሆኑ፡በዙሪያው፡እንዲ ኖሩ፡የሚፈልጋቸው፡የዚሁ፡ሃይማኖት፡አማኞች፡የሆኑትን፡ብቻ፡የሚመርጥና፡የተለመደ፡ተግባ ሩም፡መሆኑ፡ይነገራል።የጴንጤ፡ሃይማኖት፡ያስተማረው፡ማልቀስ፣አስተሳሰብ፡የጐደለው፡ደካ ማ፡ወሳኝነትና፡በትግሬ፡ወያኔዎች፡ፍርሃት፡እንዲዋሃደው፡የሚያደርግ፡ነው።ጨካኝነትና፡ነፍሰ፡ገዳይነት፡ከትውልድ፡የወረሰው፡ነው።አረመኔው፡ዘረ፡ከሃዲ፡መለስ፡ይሠራ፡የነበረውን፡ግፍ፡ለ ማጠናከር፡መዘጋጀቱ፡አስገርሞናል።

*https://www.youtube.com/watch?feature=player_embedded&v=3DosRAVmkBc መልካም፡መሪ፡እንደ፡ነበረ፡ሁልሉ፡“ራዕዩ፡ሳይበረዝ”፡እሥራ፡ላይ፡ለማዋል፡ማስሰቡ፡በተዋሃዱት፡ጠባዮቹ፡ምክንያት፡እንደ፡ሆነ፡አያጠራጥርም።በጠቅላይ፡ኃላፊነቱ፡የአስ ተዳደር፡አመራር፡ለውጥ፡ያድርጋል፡ብሎ፡ማሰብ፡ከንቱና፡ዘበት፡ነውና፡“ታጥቦ፡ጭቃ”፡እንደ፡ሆነ፡የታወቀ፡ነው።ለኢትዮጵያ፡ሀገራችን፡ቸሩ፡አምላካችን፡የሚጠብቃት፡በመሆኑ፡ሐሳባቸው፡እሩቅ፡የነበረ፡ሁለት፡ከሃዲዎችና፡የሕዝብ፡ጠላቶች፡በአንድ፡ግዜ፡አከታትሎ፡ሳያስቡት፡እንደ፡ወሰዳቸው፤የቀሩትንም፡የትግሬ፡ወያኔ፡ጥርቃሞች፡ለሀገሪቱና፡ሕዝቧ፡አንድነት፡መጠናከር፡ጠንቅ፡ስለ፡ሆኑ፡በቅርቡ፡ይጠራርጋቸዋል። በማለት፡እምነታችን፡ጽኑዕ፡ነው።አቶ፡ኃይለማርያ ም፡ደሳለኝ፡ዕድሜው፡፵፯፡(ዐርባ፡ሰባት)፡ዓመታት፡ሲሆን፣ዐማራን፡መጥላቱ፡ያስገርማል።የዐ ማራን፡አስተዳደርና፡አመራር፡ሳያውቀው፡በወታደሩ፡ደርግ፡የአገዛዝ፡ዘመን፡አድጎና፡ተምሮ፡አሁን፡የወያኔ፡አገልጋይ፡በመሆኑ፡አይፈረድበትም። ሆኖም፣የአገሩንና፡የሕዝቧን፡ታሪክ፡አያውቅም።ቢያውቅ፡ኖሮ፡በቅድሚያ፡ሕዝቧ፡ተከብሮ፡የአገሩ፡አንድነት፡እንዲጠበቅ፡ጥረት፡አደርጋለሁ፣ከወደቀችበት፡ለማንሳት፡እሞክራለሁ፡የሚል፡ሐሣብ፡ሊኖረው፡የሚገባውን፡ዕቅ ድ፡በመግለጽ፡ፈንታ፡እንዴት፡የከሃዲውን፡የመለስን፡ዚናዊን፡ራዕይ፡ሳይበረዝ፡እቀጥላለሁ፡

ገጽ፡፫-፫፡-

ለማለት፡ደፈረ?።ስለዚህ፡ሁልሉ፡ነገር፡ለእርሱ፡“ሲያዩት፡ያምር፡ሲይዙት፡ይደናገር”፡ሆኖ በታል።

እግዚአብሔርን፡አማኙ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡መንግሥት፡አልባ፡እራሱን፡በራሱ፡እያስተ ዳደረ፡ለሃያ፡አንድ፡ዓመታት፡ቆይቷል።አሁን፡አቶ፡ኃይለመርያም፡በአሻንጉሊትነት፡ነፃነትና፡ፍትሕ፡ሊመራ፡ይችላል፡ከማለት፡በአዲስ፡አበባ፡የመሬት፡ውስጥ፡ነዋሪዎች፡አስተዳደር፡የበለጠ፡ነፃነት፣ሕጋዊነትና፡ፍትሐዊነት፡አልለው።የሰው፡ልጆች፡እንደ፡አይጥ፡ጉድጓድ፡ውስጥ፡እየወለ ዱ፡የሚኖሩበት፡ሀገር፡በትግሬ፡ወያኔዎች፡የችጋርና፡ሰቆቃ፡አስተዳደር፡ብቻ፡ነው።“....በነጻ ወሊድ አገልግሎት ያገኘች እናት የምትታረሰው በወጉ ነው። በርግጥ የጠረን መቀየርና አንዳንድ የጽዳት ችግሮች ቢኖሩም መላው የመሬት ውስጥ ነዋሪዎች አራስ እህቶቻቸውን ለማረስ የሚያደርጉት ትብብርና በተግባር የሚያቀርቡት ቁስ ከየትኛውም ዜጋ የሚተናነስ አይደለም። ራሳቸውን የቻሉ ማኅበረሰቦች



*፩፡- በጀግናው፡ቀኝ፡ጌታ፡ዮፍታሔ፡ንጉሤ፡የተነገረ፡ቅኔ።

“ኢትዮጵያ፡ሀገሬ፡ሞኙ፡ነሽ፡ተላላ፣
የሞተልሽ፡ቀርቶ፡የገደለሽ፡በልላ”።*፩፡-

በመሆናቸው ማህበራዊ ግንኙነታቸው ከጉድጓዱ አንድ ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ ያሉትን አንድ ላይ የሚያሳትፍ በመሆኑ የጎላ ችግር አያጋጥምም።.........የመሬት ውስጥ ነዋሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ ማንኛውም ሰላማዊ ሰው ላይ ለዝርፊያ በሚል ጉዳት እንዲደርስ አይፈቅዱም። አንድ ዝርፊያና ለዝርፊያ ሲባል አደጋ ቢደርስ ፖሊስ ከሚኖሩበት ጉድጓድ ውስጥ ስለሚያባርራቸው ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ሰው ሲመለከታቸው ሌባ አድርጎ ያስባቸዋል። ላያቸውን በመመልከትና በጎዳና ላይ ስለሚታዩ አይታመኑም። ከቢሮና ከሚሰሩበት ቦታ፣ አየር በአየር ሲያጭበረብሩ የሚውሉ ወሮበሎች የጎዳና ተዳዳሪዎችን ሌባ አድርገው ይስሏቸዋል።.........የሰከሩ ሰዎች ሲያጋጥሙዋቸው በክልላቸው ተዘዋዋሪ ሌቦች አደጋ እንዳያደርሱባቸው ጥበቃ ያደርጋሉ። ከቻሉም ይንከባከባሉ። አንዳንዴም እስኪነጋ አስጠግተው ይሸኛሉ። .............. በየቢሮውና በየቀበሌው ተሰግስገው ከድሃ ህዝብ ላይ ከሚዘርፉት ይልቅ እነርሱ የተሻለ ስብዕና አላቸው። በዘመቻ ከሚኖሩበት ዋሻ ያባርሩናል ብለው እንጂ ጨለማን ተገን በማድረግ ብዙ ብዙ ድርጊቶች በፖሊስ፣ በደህንነት ሃይሎችና በሹማምንቶች ሲፈጸሙ ስለማየታቸው ጥርጥር የለውም”። *(http://www.goolgule.com/)

የትግሬ፡ወያኔና፡ኢሕአዴግ፡ይወርዳሉ።ዘራፊዎቹ፡ይቀጣሉ።ኢትዮጵያም፡ለዘላለም፡አንድነቷ፡ ተከብሮ፡ትኖራለች።

## ኢትዮጵያና፡ሕዝቧን፡እግዚአብሔር፡ባርኮ፡ያጠንክር። በክብረ፡ነፃነቷም፡ለዘላለም፡ትኑር።አሜን።

ከዜናማርቆስ፡መርሐ፣
ሰሜን፡አመሪካ።
እ፡ጦማር፡- E-mail:- zienamarqos14@gmail.com



*፩፡- በጀግናው፡ቀኝ፡ጌታ፡ዮፍታሔ፡ንጉሤ፡የተነገረ፡ቅኔ።